# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 298 ጥር 16 2006 ገጽ 1


**የወያኔ አገዛዝ በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እስካልተተካ ድረስ የኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ መደህየቱ፤ ጥቂት ሀብታሞች ደግሞ በብዙህኑ ድህነት መበልፀጋቸው አይቀርም። የወያኔ ውሸቶች ለኢትዮጵያ ድህ ምግብና መጠለያ አይሆኑለትም። ለኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ማምጣት የምንችለው ወያኔን አስወግደን በምትኩ ለሕዝብ ሁለተናዊ እድገት የሚጨነቅ መንግሥት መምረጥ ስንችል ብቻ ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አሁንም መሬት መንጠቁን እንደቀጠለበት መሆኑ ተሰማ

በፋሽስት ወያኔ የሚታዘዘው የአዲስ አበባ መሬት ልማትና ከተማ ኤጀንሲ የሚባለው ዘራፊ ተቋም እንደለመደው በልማት ስም ቁጥራቸው በርከት ያሉ የአዲሳባ ኗሪዎችን ከቤታቸው በማፈናቀል መሬታቸውን ለመቸብቸብና የአገዛዙን ካዝና ለመሙላት እንዳቀደ ተጠቆመ። በዚሁ ሳቢያና መሬት ነጠቃን ተከትሎ በሚመጣ ሙስና የጉጅሌውን ተላላኪ ካድሬዎች ኪስ በማድለብ ህጋዊውን ዜጋ ገንዘቡን በማራቆትና የቤት አልባ በማድረግ የማባረሩ እንቅስቃሴ መጀመሩ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱም ተያይዞ ተጠቅሷል።

የአሁኑ ዘረፋ ኢላማ ያነጣጠረባቸው ቦታዎች በካዛንችስ ልዩ ስሙ “ካዛንችስ ሰፈር”፣ አፍሪካ ህብረት እንዲሁም ሆቴል ዲ አፍሪክ አካባቢ ያሉ መኖሪያ ሰፈሮችን ጨምሮ በአጠቃላይ እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ በ4 ክፍለ ከተሞች በ 180 ሄክታር የሚገመት ቦታ ላይ የሚኖሩ ህጋዊ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ቦታቸውን ለመቀማት የዝርፊያ ዝግጅቱን መጠናቀቁን ለማወቅ ተችሏል። የአዲስ አበባ መሬት ልማትና ከተማ የዝርፊያ ኤጀንሲ እስካሁን ድረስ 30 ሄክታር የሚሆን ቦታ ላይ ያረፉ ቤቶችን ለልማት በሚል ዲስኩር በማፈራረስ ዜጎችን ለከፍተኛ የኑሮ ቀውስ እንደዳረገም ለማወቅ ተችሏል።

ይህ ዘረኛ የጉጅሌ አገዛዝ በቤት ልማት ስም እስካሁን ባካሄደው የተደራጀ መጠነ ሰፊ ዝርፊያ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጐችን ቤት አልባ በማድረግ ያለምንም ተተኪ ቦታና ተመጣጣኝ ካሳ በማፈናቀል ለጐዳና ህይወት መዳረጉን እየተከታተልን መዘገባችን ይታወሳል።

## የአማራ ክልል ወጣቶች የትጥቅ ትግሉን በስፋት እየተቀላቀሉ እንደሆነ ታወቀ

ህወሃት መራሹ አገዛዝ እንደ ፈረስ የሚጋልበው ብአዴን በክልሉ ወጣቶች እምነት ማጣቱን በመግለጽ ጉጅሌው ሽብርተኛ ብሎ ከፈረጃቸው ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ፈጥረው በስፋት የሚንቀሳቀሱት ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንደከተተው አመነ። የጉጅሌው አገዛዝ በሁሉም የአማራ ክልል ወረዳዎች ባካሄደው የብአዴን ቱልቱላ ካድሬዎች ስብሰባ፤ ወጣቶች መረጃ በማስተላለፍ እና ለአሸባሪዎች መሳሪያ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል ረገድ በስፋት እየሰሩ መሆናቸውን እንደተደረሰበት በመግለጽ ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት ይኖራቸል ብለው የሚጠረጥሩት ሁሉ እንዲታፈሱ የተለመደውን የማስፈራርያ ዲስኩር አሰምቷል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በፋሽስቱ ወያኔ ክልሉን እንዲመራ የተሾመው አሻንጉሊቱ ገዱ አንዳርጋቸው ድርጅቱን ጨምሮ ክልሉን እየከዱ እየኮበለሉ የሚጠፉት ወጣቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር ገና ወደ ወያኔ ዋና ታዛዥነት በተሻገረበት ማግስት ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደከተተው ያመላከተ ንግግር ማድረጉን የውስጥ ዘጋብያችን አድርሶናል። የጉጅሌው አገዛዝ መለዮ የሆነው በክልሉ ውስጥ የተንሰራፋው ከፍተኛ ዘረፋና ሙስና፣ ጭቆና አፈናና ግድያ መባባስ የድርጅቱን አባላትና ወጣቶችን ለከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ በመዳረግ በከፍተኛ ወኔ ለትግል እያነቃቃቸው እንደሆነ በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

## በቦረናና በቡርጂ ብሄረሰብ መካከል እያገረሸ የሚቀሰቀሰዉ ግጭት አልበረደም

የወያኔ ዘረኞች አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ የገነቡት የዘርና የጎሳ አጥር በፈጠረዉ ቀዉስ የተነሳ እርስ በእረስ መጋጨትና መተራመስ የጀመሩት የቦረናና የቡርጂ ማህበረሰብ አባላት በመካከላቸዉ መግባባት ሊፈጠር ባለመቻሉ ዛሬም ድረስ እርስ በእርስ እየተጋጩ መሆኑን ደቡብ ክልል ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። በቅርቡ በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል የተነሳውን ግጭት ተከትሎ ከ4 ሺ በላይ ነዋሪዎችም ቀያቸውን ጥለው የተተፈናቀሉ ሲሆን ችግሩን እናበርዳለን በሚል ከፍተኛ የአካባቢዉ መንግስት ባለስልጣናት ወደ ቦታው በመሄድ ለማረጋጋት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም፣ ችግሩ ጭራሽ አገርሽቶበት ከ1ሺ በላይ የቡርጂ ጎሳ አባላት አካባቢውን ለቀው ወደ ደቡብ ክልል ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ የወጣት ኢትዮጵያዉያንን ህይወት ለመገበር አሁንም ሶማሊያ ገባ

ያለ ህዝብ እውቅና እና ፈቃድ በሶማሊያ ሃገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት እና ወታደር በመላክ ለበርካታ ኢትዮጵያዊያን ወታደሮች ሞት ተጠያቂ የሆነው የወያኔ አገዛዝ አሁን ደግሞ ጦሩ የአፍሪካ ህብረትን በይፋ እንዲቀላቀል እና ተጨማሪ ጦር ወደ ሶማሊያ መላኩን በተመለከተ በዚህ ሳምንት ከፍተኛ መነጋገሪያ ዜና ሆኗል። የወያኔ አገዛዝ አልሸባብን ለመውጋት እና አሸባሪነት ለማጥፋት ነው ጦር ሶማሊያ የላኩት እያለ ቢቀባጥርም ሶማሊያ ገብተው ያላግባብ የህይወት መስዕዋትነት የከፈሉት ውድ የኢትዮጵያ ልጆችን በተመለከተ በይፋ ለህዝቡ ያወጣው መረጃ የለም።የወያኔ አገዛዝ አሁንም በድጋሚ የህዝብን ፈቃድ ሳይጠይቅ ጦሩ የአፍሪካ ህብረትን እንዲቀላቀል አድርጓል። የፖለቲካ ተንታኞች እንደገለጹት የወያኔ ጦሩ በቋሚነት በሶማሊያ መስፈሩ እየተዳከመ ያለውን አልሸባብ የበለጠ ሊያጠናክረው ይችላል ብለዋል ምክንያቱም አሸባሪነትን እዋጋለሁ በማለት ዓለምዓቀፉን ማህበረሰብ እያደናበረ የሚገኘው ወያኔ የአልሸባብ መጥፋት በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ሚና እንደሚያቀዘቅዝበት እና እርዳታ እንደሚያሳጣው ያምናል ብለዋል። የወያኔ ሰራዊት ላለፉት 8 ዓመታት በሶማሊያ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ሲሆን ጦሩ ሶማሊያን መቼ ለቆ እንደሚወጣ የሚታወቅ ነገር የለም።

## ወያኔ አዲስ አበባ ዉስጥ ዘጎችን እያፈሰ ማሰሩን ቀጥሎበታል

የዘረኛዉ ወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለከተሞች ዉስጥ በመኪና ስርቆት፣ ማጅራት በመምታትና ሌሎችም ወንጀሎች መፈጸማቸውን በጥናት ደረስኩባቸዉ ያለቻዉን ከሁለት መቶ ሃምሳ በላይ ዜጎችን አስሮ እያንጋለታ መሆኑን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልነኢ ዜና ገለጹ። ግለሰቦች ወንጀል ስለመፈጸማቸዉ ከታሰሩና በሱ ቁጥጥር ስር ከወደቁ በኋላ ማስረጃ የሚሰበስበዉ ወያኔ ተያዙ የተባሉትን ተጠርጣሪዎች እስካሁን ድረስ ፍድር ቤት አለማቅረቡን በስልክ ያናገርናቸዉ የተጠሪጣሪዎቹ ቤተሰቦች ተናገሩ። ወያኔ ለሰባትና ስምንት አመታት በተከታታይ በድርብ አኃዝ አሳደግኩት የሚለዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ለአገሪቱ ወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር ባለመቻሉ አዲስ አበባን ጨምሮ በብዙ የአገሪቱ ከተማዎች ስርቆትና ሌሎችም የተለያዩ ወንጀሎች ነዋሪዉን እንዳስመመረሩት ብዙ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ይናገራሉ;፡

አዲ አበባ ውስጥ ውስጥ ዘመናዊ ስለኮችን በአደባባይ መያዝና፣ ውድ ጌጣጌጦችን አድርጎ መጓዝ አደጋ እየሆነ መምጣቱን ነዋሪዎች ይናገራሉ። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ፖሊስ እስከዛሬ ድረስ ዝም ብሎ ቆይቶ አሁን እርምጃ መውሰዱ የሚያሳየዉ ለህዝብ መጨነቁን ሳይሆን ከመጪዉ ምርጫ ጋር በተያያዝ ረብሻና አለመረጋጋት ይፈጠራል ከሚል ስጋት ነዉ በማለት የወያኔን እርምጃ አጥብቀዉ ይተቻሉ። ከዚህ በተጨማሪ አንድአንድ አስተያየት ሰጪዎች ወያኔ በመጪው ምርጫ ሁከት ይፈጥራሉ ብሎ የሚያስባቸውን ሰዎች በወንጀለኛ ስም ማሰር መጀመሩም ሊሆን ይችላል በማለት አስተያየት ይሰጣሉ።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡ የዉጭ ባለሃብቶች ስራ አለመጀመር ወያኔን አስደነገጠ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በኢንቨስትመንትና ንግድ ስራዎች ላይ ለመሰማራት በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በኩል ተመዝግበዉ ከኤጀንሲው ፈቃድ ከወሰዱ ከ6ሺህ 500 ፕሮጀክቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ ወደሥራ ባለመግባታቸው የወያኔ አገዛዝ የኢንቨስትመንት ፈቃዳቸውን ለመሰረዝ መወሰኑን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ። ይህ አዲስ አበባና ዉስጥ ከሚገኙ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች የደረስን ዜና ተግባራዊ ከሆነ ከ 2 ሺህ 500 በላይ ፕሮጀክቶች ቀድም ሲል የተሰጣቸዉ የስራ ፈቃድ እንደሚሰረዝ ታውቋል።

ከኤጀንሲው የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው የቱርክ፣ የሕንድና የቻይና ባለሃብቶች በአገሪቱ በግብርና በማኒፋክቸሪንግ እና በአገልግሎት ዘርፎች ለመሰማራት በቅደም ተከተል ፍላጎት እያሳዩ ቢሆንም በተለይ የአውሮፓና አሜሪካ ባለሃብቶች መካከል ብዙዎቹ ፈቃድ ከወሰዱ በኃላ በዚያው የውሃ ሽታ ሆነው የሚቀሩበት ሁኔታ መከሰቱ መንግስትንአሳስቧል። ባለፉት ሶስት ዓመታት ብቻ 51 ቢሊየን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 2ሺህ 164 ያህል ፕሮክቶች ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም እስካሁን ወደማምረት ደረጃ የተሸጋገሩት 637 ያህል ፕሮጀክቶች ብቻ እንደሆኑ የኤጀንሲው መረጃ ያሳያል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ የውሸት ዘገባዎች ሲጋለጡ

“አክስፋም” በመልካም ሥራቸው ከታወቁ ትላልቅ ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አንዱ ነው። በቅርቡ አንድ መቶ ሀያ አምስት አገሮችን ያካተተ ከምግብ አቅርቦትና አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ጥናት ውጤት ይፋ አድርጓል። ጥናቱ አራት ዝርዝርና አንድ አጠቃላይ አመላካቾች አሉት።

1. አመላካች አንድ: የምግብ እጥረት

   ይህ አመላካች “በየአገሮቹ ምን ያህል ለበላተኛው የሚበቃ ምግብ አለ?” የሚለውን ይለካል። በጥናቱ ውጤት መሠረት በምግብ እጥረት እጅግ የተጎዱ የመጨረሻዎቹ አስር አገሮች የሚከተሉት ናቸው: - ቡሩንዲ፣ የመን፣ ቻድ፣ ኢትዮጵያ፣ ማዳጋስካር፣ ናይጄሪያ፣ ላኦስ፣ ባንግላዴሽ፣ መካከለኛዉ አፍሪካ ሪፑብሊክ እና ህንድ። ኢትዮጵያ አገራችን ከመጨረሻ አራተኛ ናት።

2. አመላካች ሁለት: ለምግብ የመክፈል አቅም (Affordability)

   ይህ አመላካች “የአገሩ ሕዝብ በአገሩ ዋጋ ምግብ ገዝቶ ለመብላት ምን ያህል አቅሙ ይፈቅድለታል?” የሚለውን የሚመልስ ነው። አሁንም ከመጨረሻ እንጀምር። አንጎላ፣ ዚምባቡዌ፣ ቻድ፣ ጉያና፣ ኢትዮጵያ፣ ናይጄሪያ፣ ኮንጎ፣ ኬንያ፣ ጋምቢያ እና ኢራን የየአገሩ ሕዝብ ምግብ መሸመት የሚቸገሩባቸው አገሮች ናቸው። አገራችን ኢትዮጵያ ከመጨረሻ አምስተኛ ናት።

3. አመላካች ሶስት: የምግብ ጥራት

   ይህ የምግብ ይዘትንና የአያያዝ ንጽህናን የሚመለከት ሲሆን ኢትዮጵያ፣ ማዳጋስካር፣ሞዛምቢክ፣ ቻድ፣ ቶጎ፣ ዛምቢያ፣ ማሊ፣ ናይጄሪያ፣ ባንግላዴሽ፣ ሌሶቶ ከመጨረሻው እስከ አስረኛ ደረጃ ይዘዋል። ኢትዮጵያ በምግብ ጥራት የመጨረሻዋ አገር ናት።

4. አመላካች አራት፡ የሰውነት ውፍረት እና የስኳር በሽታ

   ይህ አመላካች ከልክ ያለፈ ውፍረት ዓለም ዓቀፍ የጤና ችግር እየሆነ በመምጣቱ የገባ አመልካች ነው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥሩ ውጤት ያመጣችሁ በዚህ አመላካች ብቻ ነው። ኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝቧ ቀጫጫ ነው፤ የስኳር በሽታም እንደሌላው አገር የተስፋፋባት አገር አይደለችም።

5. አማካይ ውጤት

   የእነዚህ አራት አመላካቾች ድምር ውጤት አጠቃላይ ውጤትን ይሰጣል። በአጠቃላይ ውጤት: ቻድ፣ ኢትዮጵያ፣ አንጎላ፣ ማዳካስካር፣ የመን፣ ቡሩንዲ ናይጄሪያ፣ ሞዛምቢክ፣ ዚምባቡዌ፣ ሴራሊዮን ከመጨረሻ እስከ አስረኛ ወጥተዋል። ኢትዮጵያ ከመጨረሻ ሁለተኛ ነች።

ይህ ምንን ያመለክታል?

ወያኔ ባለፉት አስር ዓመታት በተከታታይ ከ11% በላይ ኢኮኖሚውን አሳድጌዋለሁ ሲለን ነበር። እድገቱ ያተኮረው ገጠር፤ ምንጩም ግብርና ነው ብሎን ነበር። ሐቁ ግን ከላይ የተመለከተው ነው።

እርግጥ ነው የወያኔ ሹማምንት በከተሞች ሕንፃዎችን ይገነባሉ፤ በገጠሮች በመቶዎች ሄክታር የሚለካ ለም መሬት ይዘው ፈጣን ገንዘብ በሚያስገኙ የአበባ፣ የጫትና የቃጫ ምርት ላይ ተሰማርተዋል። ከራሳቸውም አልፈው ሀብታም የውጭ አገራት ሸሪኮቻቸውን በአገራችን ለም መሬት ይበልጥ ያበለፅጓቸዋል። የእነሱ የግላቸው፣ የቤተሰቦቻቸው፣ የዘመዶቻቸው እና የሸሪኮቻቸው ኢኮኖሚ እየተመነደገ መሆኑን እናውቃለን። ይህን በገዛ ዓይኖቻችን የምናየው ሀቅ ነው።

ሆኖም ግን የእነሱ ኢኮኖሚ ማደግ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማደግ አለመሆኑ እናውቃለን። አገራችን ከጓረቤት አገሮች ጋር ስትነፃፀር ወደ ኋላ እየቀረች መሆኑ ያንገበግበናል። በቅርቡ አክስፋም በጥናት ያረጋገጠዉ የኢትዮጵያ ገበሬዎች በየቤታቸው ከወዳጆቻቸው ጋር በምስጢር የሚያወሩትን እውነት ነው።

ከሳምንት በፊት ደግሞ “ኢኮኖሚክ ኢንተለጀንስ ዩኒት” የተሰኘው ታዋቂ የምርምር ተቋም አንድ የጥናት ውጤት ይፋ አድርጎ ነበር። በዚህ የጥናት ውጤት መሠረት በዓለም በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ያሉ አስር አገሮች በቅደም ተከተል ሞንጎሊያ፣ ሴራሊዮን፣ ቱርክሜንስታን፣ ቡታን፣ ሊቢያ፣ ኢራቅ፣ ላኦስ፣ ቲሞር-ሊስቲ፣ ኤርትራ እና ዛምቢያ ናቸው። በዝርዝሩ ውስጥ ኢትዮጵያ አገራችን የለችበትም።

በዓለም አቀፍ መድረኮችም የወያኔ መረጃዎች ውሸትነት እየተጋለጡ መሆናቸው በጎ ምልክት ነው። የሚያሳዝነው ግን ይህንን ሀቅ የሚያዉቁ ምዕራባዉያን ለጋሽ አገሮች አሁንም ወያኔን እየረዱና እየደገፉ ሥቃያችን የሚያራዝሙብን መሆኑ ነው።

ለዚህም ነው ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዘላቂ መፍትሔ ሊመጣ የሚችለው በአገራችን መሠረዊ የሆነ የአስተዳደር ለውጥ ሲኖር ነው ብሎ የሚያምነው። የወያኔ አገዛዝ በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እስካልተተካ ድረስ የኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ መደህየቱ፤ ጥቂት ሀብታሞች ደግሞ በብዙሀኑ ድህነት መበልፀጋቸው አይቀርም። የወያኔ ውሸቶች ለኢትዮጵያ ድሀ ምግብና መጠለያ አይሆኑለትም። ለኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ማምጣት የምንችለው ወያኔን አስወግደን በምትኩ ለሕዝብ ሁለተናዊ እድገት የሚጨነቅ መንግሥት መምረጥ ስንችል ብቻ ነው።

ስለሆነም ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በውሸት እድገት እያደናቆረን፤ በተግባር ግን እያደኸየን ያለውን ዘራፊውን ወያኔን አስወግደን በሕዝብ ነፃ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት እንዲኖረን ትግላችን እናጠንክር ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የድምጻችን የሰማ ታጋዮች ድምጻቸዉን አሰሙ

በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት አርብ ቀን ወያኔ በሃይማኖታዊ ጉዳዮቻቸው የሚያደርገውን ዘርፈ ብዙ ጣልቃ ገብነት የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ቆይተዋል፡ የእስልምና ተከታዮቹ ከአንድ አመት ለበለጠ ጊዜ ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ የነበረ ቢሆንም በመሃል ለተወሰነ ጊዜያት ተቃውሞ ማሰማቱን አቁመው ነበር።

አሁን እንደ አዲስ በተጀመረው እና 730 ቀናት ለሃይማኖት ነጻነት በሚል ርዕስ በተጠራው የአርብ ጁምአ ተቃውሞ በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ በ100 ሺህዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ተገኝተው የወያኔ አገዛዝ በሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብቶ የሚፈተፍተውን ሴራ ሲቃውሙ ውለዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የእምነት ነጻነታቸውን ለማስከበር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ መሪዎቻቸው እንዲፈቱ ጥያቄ ቢያቀርቡን የወያኔ አገዛዝ መሪዎቹን አሸባሪ የሚል ቅጥያ በመስጠት የጥፋተኛነት ውሳኔ ወስኖባቸዋል።

## በቦረናና በቡርጂ ብሄረሰብ መካከል . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ተገድደዋል። ከሜጋ ከተማ ወደ 12 ኪሎሜትሮች ርቀው ከሚገኙት ጎዳቤሮ፣ ባታንጋላዶ እና አላ ጫፉ በሚባሉት ቀበሌዎች ይኖሩ የነበሩ የቡርጂ ማህበረሰብ አባለት መሬቱ የእናንት አይደለም ተብለው እንዲወጡ መደረጋቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመልክቷል። በቅርቡ የተነሳው ግጭት መነሻ አንድ የቦረና ሰው ተገድሎ መገኘቱ ሲሆን፣ የልዩ ዞኑ ምክትል አዛዥ የሆኑት አቶ ሊባን አሬሮ እጅ እንዳለበትም ይገልጻሉ። አቶ ሊባን የተባሉት ባለስልጣን በምን ምክንያት እንደሞተ ያልታወቀውን ሰው ቡርጅዎች ገድለውታል ብለው የአካባቢውን ሰው ቀስቅሰው ወደ ግጭት እንዲያመራ አድርገውታል በማለት ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጸው ነበር።

በቅርቡ ኬንያ ውስጥ በገብራና በቦረናዎች መካከል በተፈጠረው ግጭት ቡርጅዎች ከገብራዎች ጎን ቆመው ቦረናዎችን ወግተዋል በሚል በሁለቱ ህዝቦች መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ማድረጉን ገለልለተኛ ወገኖች ይናገራሉ። ባለፉት 3 ቀናት የታየውን መፈናቀል በተመለከተ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ አካባቢው ሰው እንደተናገሩት፣ ቡርጂዎች ከብቶቻቸውን እየተቀሙ ቦረናን ለቀው ወደ ደቡብ ክልል ተሰደዋል። እስከ ትናንት ድረስ ከ1 ሺ 200 በላይ ቡርጂዎች መሰደዳቸውን ገልጸዋል።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በኢንቨስትመንት ህጉ መሰረት አንድ የውጪ ባለሃብት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከወሰደ በኋላ በየስድስት ወሩ ለኤጀንሲው ሪፖርት በማድረግ በየአመቱ ደግሞ ፈቃዱን ማደስ የሚጠበቅበት ሲሆን ይህ ካልተሟላ ግን ከሁለት አመታት በኋላ ፈቃዱ ይሰረዛል ይላል።

ይህም ሆኖ ግን ብዙዎቹ ባለሃብቶች መሬት ተረክበው ጭምር ወደ ስራ አለመግባት፣ ሳያሳውቁ ዘርፍ መቀየር፣ መሬት በመሸጥ በመለወጥ፣ከመንግስት ባንኮች ተበድሮ በመሰወር ወንጀሎች ውስጥ ጭምር መገኘታቸው የኤጀንሲው መረጃ ይተነትናል። መንግስት በሁለት ዓመት ውስጥ ፈቃድ መሰረዝ ቢችልም ከ10 ኣመታት በላይ ብዙዎቹን መታገሱን መረጃው ጠቁሞ ከዚህ በላይ መታገስ ስለማይቻል ፈቃዳቸው እንዲሰረዝ መወሰኑና ከዚህም በሃላ እንዲህ ዓይነት የማስታመም ዕድል እንደማይሰጥ ዝቷል። ብዙዎቹ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱ በሃላ እንደመሬት፣ የባንክ ብድር የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለመፈጸም ከፍተኛ መንገላታት እንደወሰደባቸው፣ ለፕሮጀክት ያሰቡትን በጀት ለጉቦ ጭምር ለመክፈል መገደዳቸውን በየጊዜው በመግለጽ ቅሬታቸውን ሲያቀርቡ የቆዩ ሲሆን ጥቂት የማይባሉትም በመሰል ችግሮች ከስረው ወደአገራቸው መመለሳቸው፣ አንዳንዶቹም ወደኬንያና ኡጋንዳ ለመሄድ መገደዳቸውን መግለጻቸው የሚታወስ ነው። በአሁኑ ወቅት የህንድ እና የቻይና ባለሃብቶች ከከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በመሞዳሞድ በተለይ በብዛት በተሰማሩባቸው በግብርና፣ በማኒፋክቸሪንግ፣ በመንገድ ግንባታ፣ በቴሌኮም እና በኤሌክትሪክ ሃይል ዘርፎች ከፍተኛ ህገወጥ ጥቅም እያገኙ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

# የወያኔ ነፍስ በበረከት ስምዖን በኩል ስትቃዥ

( በነፃነት ዘለቀ - ክፍል 1 )

አንደኛው መስከረም ጠብቶ ሌላኛው መስከረም እስኪጠባ ድረስ ባሉት የ365.25 ቀናት ውስጥ ስንት ጉድ መስማት እንዳለብን የሚጠቁም አሃዛዊ መረጃ ሊኖር እንደማይችል መቼም ግልጥ ነው፤ ነገር ግን የዘመናችን ኢትዮጵያ የታሪክ ጎርፍ ያመጣብን ከወያኔና መሰሎቹ በስተቀር ሌሎቻችን ያልጠበቅነው ዱብዕዳ ክስተት ምሥጋና ይንሳውና በዬቀኑ የማንሰማውና የማናየው ዕንቆቅልሽ እንዳይኖረን ሆነናል። በዚህ መልክ በተለይ ባለፉት 22.8 ዓመታት ውስጥ የታዘብነው የታሪክ ምፀትና ወኔያዊ የውሸት ስንክሳር በረጂሙ ታሪካችን ታይቶም ሆነ ተሰምቶ እንደማያውቅ ማንም ጤናማ ኅሊና ያለው ዜጋ የሚመሰክረው ይመስለኛል። ለዛሬ አንዱን የወያኔ ነጭ ውሸት እንመለከታለን።

በነገራችን ላይ ወያኔና እውነት ዐይንና ናጫ መሆናቸውን የማይረዳ ወገን እንደማይኖር እገምታለሁ። የወያኔን ተፈጥሮ ወያኔ ራሱን ጨምሮ ሁሉም ያውቃል፤ የወያኔ እውነት፣ የእውነት ግልባጭ የሆነችው ሀሰት ናት። ለወያኔ ውሸት ማለት እውነት ናት። ለወያኔ እንደእውነት የሚመርና የሚያቅር ነገር የለም። በተቃራኒው ደግሞ ለወያኔ እንደሀሰት የሚጣፍጥ ምንም ነገር የለም። ወያኔና እውነት በሂሳባዊ አገላለጽ 'asymptote' ናቸው - መቼም ሊገናኙ የማይችሉ ተጻራሪ ኑባሬያት በመሆናቸው። ወያኔ የሀሰት የህግ ባል ነው፤ የሚለያዩት ወይም የሚፋቱት ከሁለት አንድኛቸው ወይም ሁለቱም ሲሞቱ ብቻ ነው። ሀሰት ግን እስከዓለም ፍጻሜ ስለምትኖር ወያኔ ካልጠፋ ከውሸታምነቱና ከሀገር አጥፊነቱ ተፈጥሯዊ ባሕርይው ሊፋታ አይቻለውም። ታሪክ ግን ሥራውን የማይረሣ ቆፍጣና ገበሬ በመሆኑ ጊዜውን ጠብቆ እነዚህን ጉግ ማንጉጎች ወደማይቀረው መቃብራቸው እንደሚሰዳቸው የታመነ ነውና መፍረስ የጀመረው የበሰበሰ ሥርዓታቸው ከነሰንኮፉ ተገርስሶ ሀገራችን በቅርቡ ነጻ እንደምትወጣ በሙሉ ልብ አምናለሁ። በዚህች መንደርደሪያ ወደሰሞነኛው የበረከት ስምዖን ውሽከታ እንለፍ።

"የኢትዮጵያ አርሶ አደር እስካሁን በተደረገለት ሥራ በሚገባ የረካ ስለሆነ ‹መንግሥት ሰልፍ ውጣ ቢለው ይወጣል፤ መንግሥት ተኛ ቢለው ይተኛል፤ ግፍ ብንፈጽም እንኳን አርሶ አደሩ ይህንን መንግሥት ይሸከመዋል እንጂ ምንም አይለውም"

ይህን የብፃይ በረከት ንግግር በዓይነቱ ልዩ የሚያደርገው የተባበሩት መንግሥታት ሰሞኑን ባወጣው አንድ ጥናታዊ ዘገባ ላይ በአፍሪካ ፈጣን ዕድገት ከሚያሳዩ አሥር ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አለመካተቷና በተጓዳኝም ይህቺው ኢትዮጵያ - ይህቺው ወያኔን በጫንቃዋ እንደምትሸከም በረከት አፉን ሞልቶ የመሰከረላት ጉደኛዋ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ጠኔ ጓዙን ጠቅልሎ ከመሸገባቸው አምስት የመጨረሻ ድሃ ሀገራት ውስጥ መመደቧ ነው - (በረከት ይህን ሪፖርት ሳያነብ መሆን አለበት ያን በህልሙ የደረሰውን ጅሎችን የማሞኛ ተምኔታዊ (utopian) ቧልታይና ድንቃይ ድርሰቱን የደሰኮረው!)። በነገራችን ላይ በአምባገነንነትና በድህነት በወያኔ መንግሥት ሳይቀር የምትታማዋ ኤርትራ በነዚህ ዘገባዎች አልተካተተችም(እንዲያውም ዘገባው ኢትዮጵያን ይግረማት ብሎ ከአሥሩ በፍጥነት እያደጉ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ አንዷ ኤርትራ እንደሆነች የገለጠ መሰለኝ)። ኢትዮጵያ ቻድን ብቻ በልጣ በአፍሪካ በርሀብተኝነት ሁለተኛ ስትወጣ ኤርትራ ከአምስቱ የባሰባቸው ሀገራት ውስጥ አልገባችም። የርሷ መግባት አለመግባት የኔ ራስ ምታት አይደለም። ነገር ግን ይህች በማዕቀብና በልዩ ልዩ የማሰቃያ መንገዶች የተወጠረች የቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት ከኢትዮጵያ የተሻለች መሆንዋን በመረጃ በተደገፈ ዘገባ የሚረዳ ጤናማ ሰው የወያኔን ሚዲያ አስችሎት እንዴት ሊከታተል እንደሚችል ይታያችሁ። ክርስቶስ ‹አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ› አለ። ወያኔም ይህችን የክርስቶስ አባባል ቀምቶ በማንሻፈፍ "አፌን በሀሰትና ዕብለት እከፍታለሁ" አለና ነጋ ጠባ የማያቅመን የሀሰት ወሬ የማይነጥፍበት አስገራሚ ፍጡር ሆነ።

መዋሸት የማይሰለቸው ‹ልማታዊው መንግሥታችን› በሚዲያው የሚያሳየን ኢትዮጵያና እኛ በግልጥ የምናያት ኢትዮጵያ ተለያይተውብን ተቸግረናል። እነሱ ‹ኢትዮጵያ በልማት ጎዳና እየተመመች ናት፤ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ራዕይ ለማሳካት በየፈርጁ የምናካሂደው የልማት ግስጋሴ ግቡን እየመታ ነው፤ የኢትዮጵያ ልማት ማንም በማይወዳደረው ሁኔታ ወደፊት እየተምዘገዘገ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችንን በማይነቃነቅ ዓለት ላይ ገምብተናል፤ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት ሳይሸራረፍ የተከበረባትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት እውን የሆነባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ ተፈጥራለች። አሁን ዋናው ጠላታችን ድህነት ነው። እሱንም እየተዋጋነው ነው...›እያሉ በቲቪያቸው እያላገጡብን ነው - ድህነትን ለመዋጋትና ለማሸነፍ ደግሞ ስንት አሥር ዓመቶች እንደሚያስፈልጉን እነሱው ናቸው የሚያውቁት፤ ለመልካም አስተዳደር እኮ አንድ የመኸር ወቅትም ትልቅ ጊዜ ነው - እንኳንስ 23 ዓመታት። ወያኔዎች ግን በድህነት ላይ እንደዛቱና ወደታሪክነት እንለውጠዋለን እንዳሉ ሦስት ዐሠርት ዓመታትን ሊደፍኑ ነው፤ አያፍሩም። በማከያው ግን ዕድሜ ለወያኔው ጉጅሌ በምግብ "ሞልቶ መትረፍረፍ" ከአፍሪካ አንዲት ሀገር ብቻ በልጠን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን የተንጣለሉ የአስፋልት መንገዶችንና በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆች የሆኑ ኢንቬስተሮች የገነቧቸውን ሕንፃዎች "እየተመገቡና እየጠገቡ" መሆናቸው እየተነገረን ነው፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ያጡ የነጡ ዜጎቻችንም ከዬቆሻሻ ገንዳዎች የሀብታም ፍርፋሪና የሙዝ ልጣጭ ለመሻማት ቀን ከሌሊት ሲራኮቱ ይታያሉ። የወያኔ ዕድገት ይህ ነው። የወያኔ ‹ልማታዊ ጋዜጠኞች›ም በበኩላቸው የሕዝቡን ሰቆቃ እንዳይመለከቱና እንዳይዘግቡ እንደአቃቂ ፈረስ ዐይኖቻቸውን በወያኔ ተከልለው በብድርና በዕርዳታ በተገነቡ መንገዶችና ድልድዮች ላይ ካሜራዎቻቸውን በመደቀን ሌት ከቀን በተመሳሳይ ዜናዎችና ሀተታዎች ማደንቆራቸውን ተያይዘውታል። እኛን እሚያሳክከን ሆዳችን ላይ እነሱ እሚያኩልን እግራችንን። የሚገርሙ ጋዜጠኞችና የሚገርም የማፊያዎች መንግሥት።

ወደበረከት ንግግር እንመለስ። እንደእውነቱ በረከት ከፍ ሲል የተናገረውን ነገር ለምን እንደተናገረው አልገባኝም። ምን ማለት እንደፈለገ ለመረዳት አስተርጓሚ ሳያስፈልግ አይቀርም። አማርኛ ቋንቋን አውቃለሁ ብዬ ደረቴን ነፍቼ እናገራለሁ። ነገር ግን ይህንን የበረከትን ንግግር እንደመሰለኝ ተርጉሜ እንዲገባኝ ጥረት አደረግሁ እንጂ በቅጡ ልረዳው አልተቻለኝም፤ እርሱም ቢሆን ጎንደር ውስጥ ብዙ ዓመታትን ስለኖረ አማርኛን ከአፍ መፍቻው ባልተናነሰ ያውቃል ብዬ እገምታለሁና ‹ምን ማለት እንደፈለገ ሳይገባው እንዲህ ያለ የተወነገዘበረ ንግግር በአደባባይ ተናግሮ የሰው መሣቂያ ለመሆን አይደፍርም› ብዬ ለማመንም በጣም ተቸገርኩ።

ይህን ንግግር በብዙ መልኩ መገንዘብ እንደሚቻል አምናለሁ፤ በአማርኛው "የጊዮርጊስን ግብር የበላ ሳይነኩት ይለፈልፋል" ወይም በሌላ ፈሊጣዊ አገላለጽ "የምላስ ወለምታ" የምንላቸው ምሥል ከሳች አባባሎች አሉ። በፈረንጅኛው "Fruedian slip" የሚባል በሥነ ልቦና የትምህርት ዘርፍ የሚጠቀስ ሐረግ አለ። ይህ ሰው የተናገረውን ከነዚህ ጽንሰ ሃሳባዊ ዕይታዎች አንጻር ብንመለከተው ወያኔ ከመጃጀቱና በወንጀል ድርጊቶች ከመጨመላለቁ የተነሣ ነፍሱ እየቃዠች መሆኗን መረዳት አያዳግተንም። አለበለዚያ ግፍ በመሥራት ላይ የቆመ የወሮበሎች መንግሥት "ገበሬው ግፍ ብንፈጽምበትም ይሸከመናል" ብሎ መናገሩ ምን ትርጉም ይኖረዋል? አንድ ጤነኛ ሰው ከመሬት ተነስቶ "በጥፊ ባጮልህና ዐይንህን በጉጠት ባወጣውም እንደማትቀየመኝ አውቃለሁ! ከኔ በበለጠ ሊያሰቃይህ የሚችል ወገን እንደሌለ ስለማውቅ ለስቃይ ለስቃይ እኔው እሻልሃለሁና ምርጫህ እኔው ብቻ ልሆን ይገባኛል" ብሎ እንዴት ሊናገር ይችላል? እንዲህ ብሎ የሚናገር ሰው ካለ ደግሞ እንደበረከት የለዬለት በሽተኛ እንጂ ጤናማ ሰው ሊሆን አይችልም። ከወፈፌና በሽተኞች ንግግር ይሠውረን። "ዱባ ካላበደ ቅል አይጥልም" አሉ? የሚገርም በረከት ነው የሆነብኝ እባካችሁን።

ይህን ንግግር በቁሙ መረዳት እንደሚቻለው በረከት ማለት ቅል ራስና እሚናገረውን እንኳን የማያውቅ ገልቱ ሰው ነው። ለመደዴ የቃላት አጠቃቀሜ ይቅርታ ይደረግልኝና እንደዚህ ያለ ድፍን ቅልና ባልጩት ራስ የኢትዮጵያ አንዱ ባለሥልጣን እንደነበረ በነገው የታሪክ መዝገባችን ሠፍሮ ሲታይ በቀጣይ ትውልዶቻችን ዘንድ በእጅጉ ከምናፍርባቸው የታሪክ ስብራቶቻችን መካከል አንዱና ትልቁ ነው። ሰው ምን ቢጃጃል እንደዚህ አይናገርም ወይም አይጽፍም፤ አለበለዚያም አብዷል ማለት ነው። "አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል" የሚባለው እኮ እንደዚህ ያለ በደናቁርት አስተሳሰብ የተለወሰ የአነጋገር ጭቅቅት ሲያጋጥም ነው። ተመልከቱልኝ፡-

"መንግሥት ሠልፍ ውጣ ቢለው ይወጣል፤ ተኛ ቢለው ይተኛል።"

ምን ማለት ነው? ገበሬውን በማስገደድም ይሁን በማታለል ሠልፍ ማስወጣት ይቻል ይሆናል። ነገር ግን እንዴት ነው እንደሕጻን ልጅ ገበሬውን በትዕዛዝ አባብሎ ማስተኛት የሚቻለው? ምን ዓይነት ዕብሪትና ትምክህት ነው? ምን ዓይነት የድንቁርና አነጋገር ነው? ለነገሩ ወያኔዎች ከአለቃቸው ከመለስ ጀምሮ ለአነጋገራቸው ደንታ የላቸውም፤ የሚያስቡት እንደጤናማ ሰው በጭንቅላት ሣይሆን እንደ አውሬ በጡንቻ ሣይሆን አይቀርም - አውሬ በጡንቻው ካሰበ። ሀገር፣ ታሪክና ወገን አለን ብለው ራሳቸው ስለራሳቸው የሚያምኑ አይደሉም፤ ባህል የላቸውም፤ ሞራል ወይም 'ethical values' ብሎ ነገር አያውቁም፤ ምናልባት ከሴቴኒዝም በስተቀር ሁነኛ ሃይማኖትም ያላቸው አይመስሉም (ለዚህም ይመስላል ወንጀለኝነት የሚያዝናናቸውና በሰዎች ስቃይ የሚደሰቱት)፤ በትውፊትና በወግ ልማድ አያምኑም፤ ባጭሩ ወፍዘራሽ የመርገምት ውጤቶች ናቸው። ከሁሉም ነገር የወጡና ከዜሮ መጀመር የሚወዱ በፈረንጅኛው አገላለጽ nihilists ናቸው - hedonist የሚል ምርቃትም ማከል ይቻላል። ታሪክን ማጥፋትና ነባር ባህልን ማውደም ያረካቸዋልና።

ወያኔዎች ማለት ባጭሩ ማሊ በምትባለዋ አፍሪካዊት ሀገር ‹አዛዋድ› በሚል ራሳቸው በፈጠሩት አዲስ ግዛት ውስጥ ፈረንሣይ ድምጥማጣቸውን እስከታጠፋቸው ድረስ ለተወሰነ ጊዜ በሼሪዓ ህግ የሚተዳደር እስላማዊ መንግሥት መሥርተው እንደነበሩት የቱዋሬግ አማፅያን የሚመስሉ ናቸው - ወያኔዎች እንደሶማሊያው አልሻባብ ዓይነትም ናቸው - ነገር ግን መንግሥት ስለያዙ ደፍሮ በአሸባሪነት የፈረጃቸው ዓለም አቀፍ ኃይል ሊገኝ አልቻለም። ለነገሩ ወያኔዎች ሀገራዊ አጀንዳ ስለሌላቸውና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ በሶማሌ ክልል በርካታ የየረር ባሬ ጎሳ አባላትን አሰረ

በሶማሌ ክልል በቀላፎ አካባቢ የሚኖሩ የየረር ባሬ ጎሳ የአገር ሽማግሌዎች ከአንድ ወር በፊት ለጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ያስገቡት የአቤቱታ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን በመድረሱ ክፉኛ የተበሳጩት የወያኔ ባለስልጣኖች ወደ አካባቢው በመንቀሳቀስ በርካታ የአገር ሽማግሌዎችን ማሰራቸው ተሰማ።ባለፈዉ ወር የአገር ሽማግሌዎቹ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በጻፉት ደብዳቤ በሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት በአብዲ ሙህመድ ኡመር እና በጄኔራል አብርሀም የሚመራው ልዩ ሚሊሺያ እየተባለ የሚጠራው ሀይል ታህሳስ 1 እና 2 በከፈተው ተኩስ በትምህርት ላይ የነበሩ ህጻናትንና ወጣቶችን ጨምሮ 47 ሰዎችን መግደሉን የሚቾቹን ስም ዝርዝር በመጥቀስ ገልጸው እንደነበር የሚታወስ ነዉ።ልዩ ሚሊሺያው ተማሪዎች በትምህርት ላይ እንዳሉ ተኩስ መክፈቱን የአገር ሽማግሌዎቹ በደብዳቤያቸው ላይ የገለጹ ሲሆን፣ የፌደራሉ መንግስት በአስቸኳይ ደርሶ እንዲታደጋቸውም ጠይቀዋል።

የየረር ባሬ ጎሳ አባላት የክልሉ መንግስት እንደ ተወላጅ ባለመቁጠር ጭቆና እንደሚያደረስባቸው በመግለጽ ራሳቸውን የማስተዳደር መብት እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ቆይተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በክልሉ መንግስት ልዩ ሚሊሺያዎችና በየረር ባሬ ጎሳ አባላት መካከል ተደጋጋሚ ግጭት ሲደረግ ከቆየ በሁዋላ ሰሞኑን መሳሪያ ለማስፈታት ወደ አካባቢው የተጓዘው የክልሉ ልዩ ሚሊሺያ ሃይል ካፍ እየተባለ በሚጠራው ትምህርት ቤት ላይ በከፈተው ተኩስ ህጻናትንና ሴቶችን ጨምሮ 47 ሰዎች መገደላቸውን የአገር ሽማግሌዎች ገልጸዋል። ጥር 11 በተቀሰቀሰው ግጭት ከቆሰሉት ከ100 በላይ ሰዎች 17 ሰዎች በህክምና እጦት መሞታቸውን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የብሄረሰቡ ተወካይ ለኢሳት ገልጸዋል።ዜናው በኢሳት መተላለፉን ተከትሎ የሚሊሺያ ሃይሉ በትናንትናው እለት 16 የአገር ሽማግሌዎችን ይዞ ማሰሩንም ተወካዩ ገልጸዋል። በጉዳዩ ዙሪያ የክልሉን ፖሊስ ኮሚሽነር ለማነጋገር ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም አልተሰካልንም።

## መፍትሄ ያጣዉ የቁጫ ወረዳ ችግር ተባብሶ ቀጥሏል

በጋሞ ጎፋ ዞን የቁጫ ወረዳ ህዝብ ተወካዮች እራስን በራስ ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ ያቀረቡት ህአዊ ጥያቄ ያስቆጣዉ የወያኔ አገዛዝ የወረዳዉን ህዝብ በመበቀል ላይመሆኑን ባለፉት ስድስት ወራት የወሰዳቸዉና አሁንም በመዉሰድ ላይ ያለዉ እርምጃ አመለከተ። በቁጫ ወረዳ ህዝብ ላይ ከመብት ጋር በተያያዘ የሚደርሰው ስቃይ እንደቀጠ ሲሆን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በፖሊሶች ወከባ የተነሳ ብዙ ሰዎች ሌሊቱን የሚያሳልፉት ጫካ ውስጥ ተደብቀዉ ነው። ፖሊሶች ሌሊት ቤት ሰብረዉ እየገቡ እንደሚፈትሹና ነዋሪዎችን እንደሚያስሩ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ መዘገቡ የሚታወስ ነዉ።

ከአንድ አመት በላይ በዘለቀው የቁጫ ችግር ከ40 በላይ የሚሆኑ የአገር ሽማግሌዎችና ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ወጣቶችም ታስረው ይገኛሉ። ከሰኔ ወር 2005 ጀምሮ እየተባባሰ ለመጣው የቁጫ ህዝብ የመብት ጥያቄ ገዢው ፓርቲ በጠረጴዛ ዙሪያ ከህዝቡ ጋር በመነጋገር መፍትሄ ከማበጀት ይልቅ በጅምላ እያፈሱ መብት ጠያቂዎችን ወህኒ ማውረድን አማራጭ አድርጎታል በማለት አንድነት ፓርቲ ከሶስት ሳምንት በፊት ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠቱ ይታወቃል። ከ1 ሺ 15 በላይ የቁጫ ህዝብ በወህኒ ቤት መገኘቱን እንዲሁም አቶ ዛሪ ዛላ የተባሉ አባወራ በአንድ የወረዳ ፖሊስ በጥይት ተመትተው ህይወታቸው ማለፉን ፓርቲው ገልጾ ነበር ።አንድነት በቁጫ ህዝብ የደረሰውን ዘግናኝ የመብት ረገጣ የሚያጣራ ገለልተኛ ቡድን እንዲቋቋም ቢጠይቅም እስካሁን መልስ አልተሰጠውም።

## ሱዳናዊ ባለሀብት የአማራን ክልል ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ

በአማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ ዉስጥ የንግድ ፈቃድ ተሰጥቶት የሲጋ ፣ የዶሮ፣ የዘይት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ከፍቶ ላለፉት አምስት አመታት በስራ ላይ የቆየዉ ሱዳናዉዉ ባለኃብት የተወራለትንና ታሰበለትን ያህል ምርት ማምረትና ማሰራጨት ባለመቻሉ የክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ባለኃብቱ ክልሉን ለቆ እንዲወጣ ወሰነ። ባለኃብቱ እስከዛሬ ያለማዉን ንብረት ለማን ይሸጥ አይሸጥ እሰካሁን ድረስ የታወቀ ነገር ባይኖርም የባህር ዳር ከተማ አስተዳደረ በባለኃብቱ ተይዞ የነበረዉን ቦታ ለሌላ አልሚ እንዲሰጥ አዟል።

የክልሉ መንግስት ለሱዱናዊው ባለሃብት ሚ/ር አሽራፍ፣ በባህርዳር የሚገኘውን የዘይት ፋብሪካ እና የግንባታ ቦታ በ65 ሚሊዬን ብር እንደሸጠላቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ ባለሀብቱ በሰራተኞች ላይ ከባድ ጥፋት ሲፈጽሙ መንግስት አይቶ እንዳላየ ሲያልፋቸው ቆይቷል። ባለሀብቱና በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት የሱዳን ዜጎች ከአባይ ወንዝና ከፖለቲካ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የደህንነት ሚስጥሮችን ለሱዳን አሳልፈው ይሰጣሉ እየተባሉ ይጠረጠሩ ነበር። ድርጅታቸውም ሁለተኛው ኢምባሲ ተደርጎ በክልሉ ባለስልጣኖች ዘንድ ይቆጠር ነበር። ድርጅቱ 234 ሰራተኞችን ያለምን ካሳ እና ተገቢ ውሳኔ ማባረሩን ተከትሎ ስራውን አቋርጦ እንዲወጣ የቀድሞው የክልሉ ኘሬዝዳንት አቶ አያሌው ጎበዜ ከአሁን በፊት ደብዳቤ ቢጽፉም፣ የፌደራል መንግስት ጣልቃ በመግባት "ቦታውን የሰጠው የፌድራል መንግስት እንጅ ክልሉ አይደለም በሚል የፕሬዚዳንቱ ማስጠንቀቂያ ውድቅ ተደርጎ ባለሀብቱ ይቅርታ እንዲባሉ ተደርጓል።

የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ድርጅቱ 50 ሚሊዩን ብር ኢንቨስት በማድረግ ጁሶችን ማምረት ጀምሮ እንደነበረ ገልጸው፣ ይሁን እንጅ ለ 2 ዓመታት በገበያ እጦት የተነሳ ምርቶቹ ለብልሸት ተዳርገዋል። የአሠራር ስርዓቱ ምቹ አለመሆኑንና መንግስት ሆን ብሎ የደህንነት ሰራተኞችን በመመደቡ ለስራው እንቅፋት መሆኑን ስራአስኪያጁ ይናገራሉ።በባለሀብቱና በክልሉ ባለስልጣናት መካከል የተጀመረው እሰጥ አገባ እየጨመረ የመጣው ባለሀብቱ ጨረጨራ ግድብ ዳር የእንግዳ ማረፊያ ቤት ለመገንባት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ ክልሉ ውድቅ በማድረጉ ነው። መንግስት ጥያቄያቸውን ከስለላ ለይቶ ባለመመልከቱ ሙሉ በሙሉ የመኖሪያ ቤት ግንባታው በፋብሪካው ውስጥ ብቻ እንዲወሰን አድርጎ ቆይቷል።መንግስት በባለሃብቱ ላይ ከኩርፊያና ከግሳጼ የዘለለ ርምጃ ሳይወስድ ቆይቶ በመጨረሻ ባለሀብቱ ክልሉን ለቆ እንዲወጣ ውሳኔ ላይ መድረሱን የክልሉ ዘጋቢያችን ገልጿል።

## አንዳንድ የደህንነት መ/ቤት ሰራተኞች ሃላፊነታችን ለአገራችን እንጂ ለስርዐቱ አይደለም አሉ

በወያኔ አገዛዝ የመረጃ አያያዝ ዘርክርክነት፤ ተቃዋሚ ኃይሎች በሚያደርጉት ያላሰለሰ የስለላ ስራና የወያኔን ዘረኛ ስርዐት በሚቃወሙ የመንግስት አካላት በኩል እየሾለኩ የሚወጡ መረጃዎች የኢህአዴግ ፓርቲና የመንግስት ህልዉና ከፍተኛ አደጋ ላይ መዉደቁን የስርዐቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ማመናቸዉ ተሰማ። የመንግስት ህልዉና አደጋ ላይ ወድቋል በሚል ከፍተኛ የመንግስትና የፓርቲ ባለስልጣኖች ግመገማ ያደረጉ ሲሆን ይህንኑ ግምገማ ተለትሎ "የደህንነት ሰራተኞች ሃላፊነታችን ለማን ነው?" የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች የደህንነት መስሪያ ቤት ለፍተኛ ባለስልጣኖችን ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ።ጥያቄውን ያነሱት በፌደራል ስር የሚገኙ የደህንነት ሰራተኞች እና ቀደም ብሎ በአቶ መለስ ዜናዊ ዘመን በትግራይ ውስጥ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ሽፋን የተቋቋመው ኤም አይ ቲ እየተባለ በሚጠራው ከመቀሌ ከተማ 9 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በተገነባው ተቋም ውስጥ ተመርቀው የወጡት የደህንነት ሰራተኞች ናቸው።

የደህንነት ሰራተኞቹ "የእኛ ሃለፊነት የአገር ደህንነትን ማስጠበቅ ነው የፖለቲካ ስርአቱን ?" በሚል ጥያቄ ያነሱ ሲሆን፣ አንድ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን" የፖለቲካ ስራ የማይሰራ ደህንነት የለም፣ የደህንነት ስራ ሲጀመር ስርአት የማቆየት ስራ ነው፤ ስርአቱን የምናቆይበት ደግሞ ፕሮፌሽናል ነው፣ በስርአቱ ላይ እምነት ማሳደር የሚጠይቅ ተግባር ነው፣ የግንቦት7ትን አስተሳሰብ የሚያቀነቅንና ስርአቱ በጉልበት መፍረስ አለበት ብሎ የሚያስብ ሰው፣ የተሰፋየ ወልደ ስላሴ አይነት የደህንነት ብቃት አለው ቢባል፣ ሞሳድ 20 አመታት አሰልጥኖታል ቢባል ስርአቱን ከማፍረስ ውጭ ደህንነቱን ሊያስጠብቅ አይችልም"፣ ስለዚህ የደህንነት ስራ ለሚሰሩ ወገኖች የፖለቲካ ወገንተኝነታቸው ወሳኝ ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል።

"የደህንነት ተቋሙ፣ ሰራዊቱና ሚዲያው በተቃዋሚዎች ዘንድ መቼውንም ቢሆን ገለልተኛ ተደርጎ አይቆጠርም" ያሉት እኝህ ከፍተኛ ባለስልጣን ፣ ገለልተኛ ማድረግ የሚባል አስተሳሰብ ያለው ካለ እንደዛ ሊሆን አይችልም፣ ሊሆን የሚችለው የተቃዋሚዎችን ሰዎች ደህንነት ውስጥ ማስገባት ነው ብለዋል።" በተለይም በተቋም ደረጃ ፤ በምህጻረ ቃል ኢንሳ እየተባለ የሚጠራው የመረጃ ደህንነት መስሪያ ቤት፤ የዜግነት እና ኤምግሬሺን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ በጀኔራል ሳሞራ የኑስ የሚመራው የመከላከያ ደህንነት፤ የአስተዳደር እና ፀጥታ፤ የፌደራል ፖሊስ፤ የፀረ ሽብር ግብረ ሃይል በእዝ ሰንሰለት በሚፈጠር ልዩነት እርስ በርስ እየተወዛገቡ ሲሆን፣ ተቋሞቹን በትክክል የሚመሩትን አካላት ለመለየት አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱና እርስ በርስ በሚፈጥሩት እሰጥ አገባ አንዱ አንዱ የሚሰራውን የማጣፋት እርምጃ እየወሰዱ መሆኑ በግምገማው ላይ ተነስቷል። የመንግስት ሚስጥሮች ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፈው እየተሰጡ በመሆኑ ሚስጢሮችን መደበቅ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ሲሉ አንዳንድ ባለስልጣኖች አስተያየቶችን ሰጥተዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ:-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ:-** በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የወያኔ ነፍስ በበረከት ስምዖን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የማንንም ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ አጀንዳ አንከርፍፈው በተባባሪነት ስለሚጓዙ ለዓለም አቀፍ ታዋቂ ኃይሎች እስትራቴጃዊ ጠቀሜታ እስከሰጡ ድረስ በአጋርነት የሚያስጠጋቸውና ሙሉ ድጋፍ የሚሰጣቸው አያጡም(ኢትዮጵያውያንን ለጊዜውም ቢሆን እያስቸገረን ያለው ይህን መሰሉ የወያኔ እስስታዊ ተፈጥሮ ነው)። እነዚያ የአልቃኢዳ የአፍሪካ ክንፍ የሆኑ አማጽያን በቲምቡክቱ ውስጥ የነበሩ ዕድሜያቸው በሺዎች ዓመታት የሚገመት የታሪክ ቅርሶችን በዶማና አካፋ እንዲሁም በግሬደር በአጭር ጊዜ የሥልጣን ቆይታቸው ውስጥ ድራሻቸውን ማጥፋታቸውን የቅርብ ጊዜ ትዝታ በመሆኑ ከዐይነ ልቦናችን ገና አልተሰወረም። ወያኔዎችም እያዋዙ በእስከዛሬው የኃይል አገዛዛቸው እጅግ በርካታ የኢትዮጵያ ቅርሶችንና ታሪኮችን አጥፍተዋል - ከሁሉም የሚብስ ጥፋታቸው ግን ከቁሣዊው ይልቅ ሥነ ልቦናዊውና ኅሊናዊ ወመንፈሣዊው አጠቃላይ ውድመት የበለጠ ኪሣራ ያደረሰብንና ለማገገምም ብዙ ጊዜ የሚወስድብን ከባዱ ጥፋት ይመስለኛል። እነዚህ ናቸው እንግዲህ ጅብ አማያውቁቀት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ እንደሚል በምናውቃቸው ምሥኪን ዜጎች መሀል ሆነው ገበሬው የነሱ እንደሆነ የሚሰብኩን። ለነገሩ ጅብ እንኳን በማያውቁት ሀገር ነበር ተናገረው የተባለውን የተናገረው። ወያኔዎች ግን ዐይናቸውን በጨው አጥበው እኛው ፊት ሸፍጣቸውንና የሀሰት ቱሪናፋቸውን ካለተቀናቃኝ ለብቻቸው በተቆጣጠሩት ሚዲያቸው ያናፋብናል።

የኢትዮጵያ ገበሬ ኑሮው ምን ይመስላል?

በአሁኑ ወቅት በወያኔ ሥርዓት እንደገበሬው የሚማረር የለም። የወያኔን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለወያኔና ወያኔያውያን ትተን እውነቱን ብቻ እናውራ ካልን የገበሬው ኑሮም ሆነ የአጠቃላዩ የሀገሪቱ ሕዝብ ሕይወት ያሳዝናል ብቻ ሳይሆን ያስለቅሳል። እኔ ይህን መልእክት የምጽፍላችሁ ዜጋ በሀገር ቤት የምኖርና አልፎ አልፎ ወደገጠር ለሥራ ጉዳይ ወጣ የምል በዚያም ምክንያት የብዙ አካባቢዎችን ነዋሪዎች ሰቆቃና የዕለት ከለት ውጣ ውረድ የምታዘብ ሰው ነኝ። ስለዚህም የምለው ነገር በስማ በለው የተገኘ ሳይሆን በራሴም ሕይወት እየደረሰ ያለ እውነተኛ ሰቆቃ መሆኑን ላስታውስ እፈልጋለሁ። የገበሬው ኑሮ ከእኛ ከከተሜዎቹ የባሰ እንጂ የተሻለ እንዳልሆነ በውነት እመሰክራለሁ።

የአንድ አምባገነን መንግሥት ትልቁ ሕዝብን የመግዣ መሣሪያ ሌላ ሳይሆን በማይምነትና በድንቁርና ሸብቦ በማስፈራራትና በማስራብ አንቀጥቅጦ ወደተናጋሪ እንስሳነት መለወጥ ነው። ወያኔም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ብትሄዱ ለይስሙላ ትምህርት ቤቶች ይሠሩ እንጂ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ባለመኖሩ መማር ካለመማር የሚለይበትን መሠረታዊ ነጥብ ፈልጋችሁ ልታገኙ አትችሉም። በመሆኑም ገበሬው ከትምህርት ርቋል፤ የጨለማ አዘቅት ውስጥም ከገባ ቆይቷል። በማይምነት አለንጋ እየተገረፈ፣ በብጥቅጣቂ እርሻ ላይ በሚዘራት አነስተኛ ሰብል እየተሰቃዬ፤ ከዚያችም ሰብል ላይ ከፍተኛ ግብር እንዲከፍል እየተገደደና ከብቱንና ንብረቱን ሸጦ ግብር እንዲያስገባ እየተጠየቀ የሚገኝ ገበሬ ወያኔን ጣዕረሞት ሲይዘው "በፍቅርና በትግስት ይሸከመዋል" ሳይሆን "የወያኔን ሬሣ ተሸክሞ ወደመቃብሩ ይሸኘዋል" ቢባል ነው ትክክለኛው። ገበሬው በቀን አንድ ጊዜም የሚቀምሰው በሌለበት ሁኔታ፣ ገበሬው የልጁን ወስፋት የሚሸንግልበት አንዳችም እህልና ጥሪት አልባ በሆነበት ሁኔታ፣ ገበሬው ከገጠር እየፈለሰ ወደከተሞች በመግባት ለወያኔ ሕንጻና ፋብሪካ ግንባታዎች የቀን ሠራተኛ እየሆነ ባለበት ሁኔታ፣ ገበሬው ልጆቹ ወደዐረብ ሀገር እየተሰደዱ ለዐረብ ጀማላ የሠይፍ እራትና የአስገድዶ መድፈር ሲሳይ እየሆኑ ባሉበት ሁኔታ፣ ገበሬው በማዳበሪያ ዕዳ የስንግ ተይዞ ሌሎቼ እያለ በሚገኝበት ሁኔታ፣ ገበሬው በአድሎአዊ የመሬት ሥሪት ምክንያት መድሎ እየተሠራበት ማለፊያው የውሃ መሬት ለካድሬዎችና ለወያኔዎች እየተሰጠ ጭንጫውና መናኛው መሬት ግን ለድሃ ገበሬ እየተሸነሸነ ባለበት ሁኔታ፣ገበሬው ከማሳውና ከመኖሪያው እየተፈናቀለ መሬቱ በልማት ስም ለወያኔ ከበርቴዎች እየተቃረጠ ባለበት ሁኔታ፣ አህያ የተጫነችውን እንደማትበላ ሁሉ ገበሬውም ያመረተውን ምርት ለዕዳ ክፍያ ሲል ለጠገቡ የወያኔ ‹ልማታዊ ባለሀብቶች› በርካሽ እንዲሸጥና ጨርቁ በላዩ ላይ አልቆ በባዶ እግሩ እየሄደ በእሾህና በእንቅፋት አሣሩን እንዲበላ ተፈርዶበት ባለበት ሁኔታ፣ ... በረከት የተናገረውን መስማት በርግጥም ተዓምር እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? በቀደመው ዘመን "እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር" ነበር ሲባል እምንሰማ። አሁን ደግሞ "እስመአልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለወያኔ"ብንል እንሳሳት ይሆን? ወያኔ ጥቁሩን ነጭ፣ ነጩን ጥቁር፤ ልቅሶን ሠርግ፣ መርዶን ብሥራት ማድረግ የሚችል ልዩ ምትሃት ያለውና በአፍ ጤፍ የሚቆላ ፍጡር ነው። ወያኔን ለሚያውቅ የወያኔ ዲስኩርና ፕሮፓጋንዳ ችግር የለውም - በወያኔ ፕሮፓጋንዳ የሚጃጃል ወያኔን የማያውቅ ወይም ማወቅ የማይፈልግ ብቻ ነው። ‹ብታምኑም ባታምኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን ከእግር እስከራሱ ጠንቅቆ ያውቀዋል!›። እናም በተለይ በአሁኑ ወቅት ወያኔ ማንንም ሊያታልል በማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ሞቶ በሞቶ እርግጠኛ ሆኜ እናገራችኋለሁኝ።

እናም ወያኔ ስለገበሬው የሚያወራውና እኛ ስለገበሬው የምናውቀው፣ ገበሬውም ስለወያኔ የሚለውና ስለራሱም ከራሱ ኑሮ የሚስተዋለው ለዪቅል መሆናቸውን ልብ ማለት ይገባል። ‹ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ› ይባላል። በረከት የሚናገረው ለሌሎች ብቻም ሳይሆን ለራሱም ሀሰት መሆኑን ማንም አያጣውም። በረከትን በማታው ‹ቱብ ጠረጴዛ› አግኝተን "ምነው ወዲ ስምዖን፣ እንደዚያ ያለ ነጭ ውሸት ማናፈስ ደግ ነው እንዴ ? ለመሆኑ አንተስ ታምንበታለህ? ኅሊናስ የሚባል ነገር የለ(ህ)ም እንዴ?" ብንለው መልሱ ቀላል ነው። "ወንድሜ፣ በፖለቲካ ኅሊና ብሎ ነገር የለም። ዋናው ማምለጥ ነው። የምታደርገውን አድርገህ፣ የምትናገረውን ተናግረህ በፊትህ ከተደቀነብህ ችግር ማፈትለክ እንጂ ስለምትናገረው ነገር እውነትነት ከተጨነቅህ ፖለቲካ ውስጥ ቀድሞውን መግባት የለብህም። በተለይ እንደኛ ዓይነቱን ችግር ለጠላትም አይስጥ ወንድሜ። የገባንበት አጣብቂኝ በቀላሉ የሚወጡት አይደለም። መጥኖ መደቆስ አስቀድሞ ነበር ወዳጄ። በደም ጨቅይተናል፤ በሙስና በክተናል፤ በዘረኝነቱም ረገድ ያጠፋነውን ጥፋትም ቆም ብለው ሲያስተነትኑት የአንገልን ሚዛን የሚያዘባና የሚያሳብድ ነው፤ ወደትግል ከገባንበት ጊዜ ጀምሮ የገደልነውና ለስደትና ለእሥራት የዳረግነው ዜጋ የኅሊና ዕረፍት እያሳጣ መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣናል፤ ለዚህም ነው ብዙዎቻችን ቢሯችን ውስጥ ሣይቀር በብርጭቆ ውስጥ መደበቅን የምንመርጠው። ሰው ወዶና ፈቅዶ ጉበቱን በመጠጥ ቦጫጭቆ ሞትን በራሱ አይጋብዝም። ታዲያ አሁን ምን እናድርግ? ነገር የተበላሸው ዱሮ ነው፤ አሁን ሁሉም ነገር ጠርዝ ከለቀቀ በኋላ ከመዋሸትና ከማምታታት ውጪ ምን አማራጭ አለን? አንድ ነገር ሲገቡበት ቀላል ነው፤ ለመውጣት ግን ከባድ ነው። የኛ ወደዚህ ሥፍራ መምጣትና አንድ ሰው ወደአደንዛዥ ዕፅ ሱስ መግባት ሂደቱ ተመሳሳይ ነው፤ ሁለታችንም እንደዋዛ እንገባለን - እንደዋዛ መውጣት ግን ለሁለታችንም ከባድ ነው።..." አዎ፣ በረከት በዊስኪ ጨዋታው ለሁነኛው ልክ እንደዚህ እንደሚያጫውተው 'subconscious'-ሉን በርቀት በማንበብ መረዳት ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ ለወደቀም ማዘን ተገቢ ነው፤ ‹ለሚወድቅ› ብላችሁ ልታሻሽሉትም ትችላላችሁ። እንደኔ ግን ወያኔዎች ሲነሱ ነው የወደቁት። ሰው ሲወለድ ነው የሞተው እንደምንል መሆኑ ነው። ወያኔዎችም ክፋትን መሥራት ሲጀምሩ፣ በቂም በቀል የተቃኘ የጥላቻ አገዛዛቸውን በስፋት ሲያጧጡፉ፣ ሀገርን ሲሸጡና ሲለውጡ፣ ምድርን በደም ረግረግ ሲሞሉ፣ አማራን ከትግሬ፣ ትግሬን ከኦሮሞ እዬለዩ አንዱን መጥቀምን ሌላውን መጉዳትን ባህላቸው ሲያደርጉ፣ ዳር ድንበርን እንዳወጣ ለባዕድ ሀገራት ሲቸበችቡ፣ ሀገርን ካለመውጫ በር ዘግተው የሚሊዮኖችን እስትንፋስ ሲዘጉ፣ ... ያኔ ነው ወያኔዎች ገና በጧት ሳይወለዱ የሞቱት። እዚህ ላይ የሞት ዓይነት ብዙ መሆኑን ልብ ይሏል። እንጂ የአሁኑ እስትንፋሳቸውማ በ"ሥልጣን" ካሳለፉት ጊዜ አንጻር ሲታይ የደቂቃዎች ያህል ጊዜ ብቻ የቀራቸው ጉድጓዳቸው የተማሰ ልጣቸውም የተራሰ ስለመሆኑ ጨረቃና ፀሐያቸውን በማየት ብቻ የምንረዳው ነው - ዘመናቸው አልቋል። ... የኔ አይደለም ...የርሱ እንጂ። የፍርድ ሂደቱና ብያኔው ከታች አይደለም - ከላይ እንጂ። ( ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል )

## አንዳንድ የደህንነት መ/ቤት ሰራተኞች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለተነሱት አስተያየቶች መልስ የሰጡት ባለስልጣኑ፣ ኢንሳ የተቋቋመውም ይህን ለመስራት መሆኑን ገልጸው፣ "አገሮች ሙሉ በሙሉ ከሳይበር ስለላ ነጻ ባለመሆናቸው አቶ ሃይለማርያምም ነጻ ናቸው ብየ አላስብም" ብለዋል። "አሜሪካኖች የምንናገረውን ሁሉ ከፈለጉ ይሰሙታል" የሚሉት እኚሁ ባለስልጣን፣ "እኛም የአቅማችንን ያክል አሜሪካኖች የሚናገሩትን ለማዳመጥ እንሞክራለን" ብለዋል። የሳይበር ስለላ ለማካሄድ ጥሩ ጅምሮች ቢኖሩም፣ ያን ያክል የምንኩራራበት ግን አይደለም በማለት ኢንሳ ያለበትን ደረጃ አመላክተዋል። ከኦሮሚያና ከደቡብ የመጡ የደህንነት ሹሞች ደግሞ "በመከላከያ የደህንነት ተቋሞች ውስጥ የአንድ ብሄር የበላይነት ጎልቶ ይታያል" በሚል ቅሬታ ያነሱ ሲሆን፣ ባለስልጣኑም "የሰራዊት ማመጣጠን ስራ በረጅም ጊዜ የሚሰራ ስራ ነው " በማለት ለመመለስ ሞክረዋል። ትግሉን መርተው እዚህ ድረስ የመጡ ሰዎችና በመከላከያ ውስጥ ያለውን የመኮንኖች ቦታ የያዙት ከአንድ አካባቢ የመጡ መሆናቸው ግልጽ ነው የሚሉት ባለስልጣኑ፣ ያም ሆኖ ከትግራይ የመጡ በርካታ ጄኔራሎች ጡረታ እንዲወጡ ቢደረግም ሂደቱ ግን ረጅም ጊዜ የሚወስድ ነው ሲሉ አክለዋል።

"የብሄር ተዋጽኦ ብቻ የአንድን ሰራዊት ጠንካራና ደካማ ጎን መገለጫ ተደርጎ መወሰድ ካለበት አደጋ አለው " ያሉት ባለስልጣኑ፣ የአንድ ብሄር የበላይነት አለ ተብሎ በአጭር ጊዜ ለማመጣጠን ብቻ በአንድ አዳር ሁሉንም ነገር መቀየር እንደማይቻል መንግስት ያምናል ሲሉ ተናግረዋል አቶ መለስ ዜናዊ በውጭ ሃይሎች ተገድለዋል ይባላልና በምን እንደሞቱ በትክክል ይነገረን በሚል ባለስልጣናት ላነሱት ጥያቄም የደህንነት ባለስልጣኑ፣ "አቶ መለስ በውጭ ሃይሎች ተገድለዋል የሚል ትክክለኛ ማስረጃ የለም በማለት መመለስ የጀመሩት ባለስልጣኑ፣ እርሳቸው የሞቱት በስራ ብዛት ተዳክመው እና ህክምናውን መቋቋም ባለመቻላቸው ነው ሲሉ ደምድመዋል።

በተያያዘ ዜናም የሃገሪቱን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል ከኢሳት ጋር በመሆን እየሰራችሁ ነው፣ ለኢሳትም መረጃ ታቀብላላችሁ ተብለው የተጠረጠሩ 5 የደህንነት አባላት በቁጥጥር ስር ውለዋል። ወጣት ሙብራቴ ታምራት፤ ወጣት ጀማል አወል፤ ጣት ደጀኔ አድማስ፤ ወጣት ሃይሉ ጨርቆስ ፤መቶ አለቃ አሰፋ አብርሃ ሰሞኑን በደህንነቶች ቁጥጥር ስር መዋላቸውን የኢሳት የደህንነት ምንጮች ገልጸዋል። በተመሳሳይ ዜናም በሃገሪቱ በ28ቱ ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙ የህወሃት አባላት ተማሪዎች እና የደህንነቶች ሃለፊዎች ግምገማ መጀመራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። በግምገማው ወቅት የኦህዴድ እና የብአዴን መሪዎች የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በመከታተል ባሰዩት ውጤት የተገመገሙ ሲሆን፣ ባለፉት ስድስት ወራት የአክሱም፤ ደብረ ታቦር እና ደብረ ብርሃን የኒቨርስቲዎች ከፍተኛ የአመጽ እንቅስቃሴ የታየባቸው በመሆኑ ልዩ የደህንነት ክትትል እንደሚያስፈልጋቸው ተወስኗል።